- እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ስለሆነ።

- የእግዚአብሔር ጥበብ ማብቂያ ስለሌለው።
- የእግዚአብሔር ጥበብ ዘላለማዊ ስለሆነ።

- የእግዚአብሔር ጥበብ ወሰን አለውን?

- የለውም።

- የእግዚአብሔር ጥበብ ወሰን የለውም።

- የእግዚአብሔር ጥበብ ማብቂያ የለውም።

- እግዚአብሔር የማያውቀው ምንም ነገር የለም።



## ትምህርት 5

1. መላእክት ከየት መጡ?

ሀ- በመጀመሪያ ሁሉንም መላእክት የፈጠራቸው እግዚአብሔር ነው።

2. እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው ደምና ሥጋ እንዲኖራቸው አድርጎ ነው?

ሀ- አይደለም።

ለ- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው መናፍስት አድርጎ ነው።

3. ታዲያ እግዚአብሔር መላእክትን ለምን ፈጠራቸው?

ሀ- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው እንዲወዱት ነው።

ለ- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው እንዲታዘዙለት ነው።

ሐ- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው እንዲያገለግሉት ነው።

4. እግዚአብሔር መላእክቱን የፈጠራቸው መልካም ወይስ ክፉ አድርጎ ነው?

ሀ- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው መልካም ብቻ አድርጎ ነው።

5. እግዚአብሔር የፈጠራቸው መላእክት ስንት ናቸው?

ሀ- እግዚአብሔር የፈጠራቸው መላእክት ብዙ ናቸው፤ ልንቆጥራቸው አንችልም።

6. በመጀመሪያ ሁሉም መላእክት የት ነበሩ?

ሀ- ከእግዚአብሔር ጋር በመንግሥተ ሰማይ ነበሩ።

7. እግዚብሔር ጠቢብና ውብ አድርጎ የፈጠረው መልአክ ማን ይባል ነበር?

ሀ- ሉሲፈር ይባል ነበር።

8. እግዚአብሔር ሉሲፈርን የፈጠረው መልካም ወይስ ክፉ አድርጎ ነው?

ሀ- መልካም አድርጎ ነው።

ለ- እግዚአብሔር መላእክትን የፈጠራቸው መልካም አድርጎ ነው።

9. ሉሲፈር ምን ሆነ?

ሀ- ሉሲፈር የራሱን ጥበብና ውበት ተመለከቶ ታበየ። እግዚአብሔርንም ከዙፋኑ ሊያወርደው ፈለገ።

10. ክፉ በመሥራት የመጀመሪያ ማን ነበር?

ሀ- ሉሲፈር ነበር።

11. ሉሲፈር ከዙፋኑ ሊያወርደው እንደፈለገ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?

ሀ- አዎን፥ ያውቅ ነበር።

ለ- እግዚአብሔር ሉሲፈር ሊያደርግ የፈለገውን ሁሉ ያውቅ ነበር።

12. ሉሲፈር ከዙፋኑ እንዲያወርደው እግዚአብሔር ፈቀደለት?

ሀ- አልፈቀደለትም።

13. ሉሲፈር ኃጢአት በመሥራት የመጀመሪያ ስለነበረ እግዚአብሔር የሉሲፈርን ስም ለወጠው። የሉሲፈር አዲሱ ስም ማን ነው?

ሀ- ሰይጣን ነው።

14. ሰይጣን ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ- ሰይጣን ማለት «ጠላት» ማለት ነው።

15. እግዚአብሔር ሰይጣንን ስለ ክፉ ሥራው በምን ቀጣው?

ሀ- እግዚአብሔር እጅግ ስለተቆጣ ሰይጣንን ከመንግሥተ ሰማይ አባረረው።



- እግዚአብሔር የፈለገውን ማንኛውንም ነገር መሥራት ይችላል።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር መሥራት ይችላል።

- እግዚአብሔር እንዴት አውቆ ከምንም ሁሉንም ነገር መፍጠር ቻለ?

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዴት መፍጠር እንዳለበት ያስተማረው አለ?

- እናንተ ወንዶች፥ ወንድ ልጆቻችሁ በልጅነት በቆሎ መትከል ስለማያውቁ እንዴት መትከል እንዳለባቸው ታስተምሯቸዋላችሁ።

- እናንተ ሴቶች፥ ሴት ልጆቻችሁ በልጅነት ምግብ ማብሰል ስለማያውቁ፥እንዴት ማብሰል እንዳለባቸው ታስተምሯቸዋላችሁ።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዴት መፍጠር እንዳለበት ያስተማረው አለ?

- የለም።

- እግዚአብሔርን ማንም ያላስተማረው ለምንድን ነው?

- በመጀመሪያ እግዚአብሔርን የሚያስተምረው ማንም በዚያ አልነበረም።

- ከመጀመሪያ በፊት እግዚአብሔር ብቻ ከኖረ እርሱን የሚያስተምረው ማንም በዚያ አልነበረም።

- በተጨማሪም እግዚአብሔርን ማንም ያስተምረው ዘንድ አያስፈልገውም።

- ለምንድን ነው እግዚአብሔር ማንም እንዲያስተምረው የማያስፈልገው?

- የእግዚአብሔር ኃይል ዘላለማዊ በመሆኑ።

- የእግዚአብሔር ኃይል ወሰን አለው?
- የለውም።

- የእግዚአብሔር ኃይል ወሰን የለውም።
- የእግዚአብሔር ኃይል ማብቂያ የለውም።

- እግዚአብሔር የማይችለው ምንም ነገር የለም።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ማድረግ ይችላል።

- እግዚአብሔር መላውን ዓለም ከምንም ፈጠረ።

- ከእግዚአብሔር የበለጠ ኃይል ያለው ማን ነው?
- ማንም።

- ሰይጣን ከእግዚአብሔር የበለጠ ኃይል አለው?
- የለውም።

- ሰይጣንን የተከተሉት አጋንንት ከእግዚአብሔር የበለጠ ኃይል አላቸው?
- የላቸውም።

- ሰዎች ከእግዚአብሔር የበለጠ ኃይል አላቸው?
- የላቸውም።

- እግዚአብሔር የማይችለው ነገር አለ?
- የለም።



16. ሰይጣንን የተከተሉ መላእክት በእርሱ ላይ ስላመጹ፥ እግዚአብሔር ስማቸውን ለወጠ። ሰይጣንን የተከተሉት መላእክት አዲሱ ስማቸው ማን ነው?
ሀ- አጋንንት።

17. ሰይጣንን የተከተሉትን አጋንንት እግዚአብሔር በምን ቀጣቸው?
ሀ- እግዚአብሔር እጅግ ስለተቆጣ ሁሉንም ከመንግሥተ ሰማይ።

18. እግዚአብሔር ሰይጣንና አጋንንቱን የቀጣቸው በሌላ በምንድን ነው?
ሀ- እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለአጋንንቱ የዘላለም ቅጣት የሚቀበሉበት እጅግ አስፈሪ ቦታ አዘጋጅቷል።

19. ያ አስፈሪ ዘላለማዊ የቅጣት ቦታ ምን ይባላል?
ሀ- ዘላለማዊ የእሳት ባሕር ይባላል።

20. ሰይጣንና አጋንንቱ አሁን ያሉት የት ነው?
ሀ- ሰይጣንና አጋንንቱ አሁን ያሉት በምድር ላይ ነው።

21. ሰይጣንና አጋንንቱ አሁን ምን እየሠሩ ነው?
ሀ-የእግዚአብሔርን ሥራ ቀንና ሌሊት እየተቃወሙ ነው።

- ከእግዚአብሔር መጽሐፍ የመጀመሪያውን ቃል እስቲ ደግመን እናንብብ፡

ዘፍጥረት 1፡1

1-በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።

- መጀመሪያው ምንድን ነው?

- መጀመሪያው ከረጅም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች የፈጠረበት ጊዜ ነው።

- በመጀመሪያው በዚህ ዓለም የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረው ማን ነው?

- እግዚአብሔር ነው።

- በዚህ ዓለም የሚገኙት ሁሉም ነገሮች በእግዚአብሔር የተፈጠሩት በመጀመሪያው ነው።

- እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከመፍጠሩ በፊት በዚህ ዓለም ውስጥ ምን ነበረ?

- ምንም ነገር አልነበረም።

- በዚህ ዓለም ምንም ነገር ካልኖረ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከምን ፈጠረ?

- እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ከምን ፈጠረ?

- እግዚአብሔር ፀሐይን ጨረቃን እና ክዋክብትን ከምን ፈጠራቸው?

- ዛፎች ባይኖሩ ቤት መሥራት ትችላላችሁ?
- አዎን፥ አትችሉም።

- እናንተ ሰዎች ከምንም ነገር ቤት መሥራት ትችላላችሁ?
- አዎን አትችሉም።

- እናንተ ሴቶች የሸክላ ዐፈር ባይኖር ማሰሮ መሥራት ትችላላችሁ?



- አዎን አትችሉም።

- እናንተ ሴቶች ከምንም ማሰሮ መሥራት ትችላላችሁ?
- በፍጹም አትችሉም።

- እናንተ ልጆች እንጨት ባይኖር መጫወቻ መሥራት ትችላላችሁ?
- አትችሉም።

- እናንተ ልጆች ከምንም መጫወቻ መሥራት ትችላላችሁ?
- አትችሉም።

- በዚህ ዓለም ምንም ነገር ካልኖረ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከምን ፈጠረ?

- ከምንም።

- ታዲያ እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት ፈጠረ?
- እግዚአብሔር ዓለምን ከምንም ፈጠረ።

- እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገር ከምንም ነው የፈጠሩት።

- እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን እንዴት አድርጎ ነው ከምንም የፈጠረው?

- እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከምንም እንዴት መፍጠር ቻለ?
- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ በመሆኑ።

- የእግዚአብሔር ኃይል ማብቂያ የሌለው በመሆኑ።